አባ ያዕቆብ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሩቅ ምስራቅ ፣ ዩናይትድ ኪንግደም ፣
አየርላንድና አካባቢው ሀገራት ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እና የዓለም የሰላም አምባሳደር
Abba Yacob
Archbishop of Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Diocese of Far East, United Kingdom, Ireland and World Ambassador for Peace

ቁጥር
Ref. No.

ቀን
Date ጳጉሜ ፫ ቀን ፳፻፲፬ ዓም
Sep 8, 2022

## መልካም አዲስ ዓመት

## ፳፻፲፭

## ከዘመነ ማርቆስ ወንጌላዊ ወደ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ አዲስ ዓመት ፳፻፲፭ ዓመተ ምሕረት ያሸጋገረን አምላክ ልዑል እግዚአብሔር ይመስገን !

ለምወዳችሁና እጅግ ለማከብራችሁ በዓለም ዙርያ ላላችሁ ለእግዚአብሔር ሕዝብና ለራሴም ደስተኛ ፣ሰላማዊና ስኬታማ የሆነ ህይወትን ለመመስረትና በፍቅር ለመኖር ያስችሉናል ብየ የማምንባቸውን ቅን በሆነ ልቡና እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር መልካም የሆኑ ሰባት ምክሮች አሉኝ።

<u>እነዚህም፡-</u>

፩/ሁሉን በፈጠረና ሁሉን በሚችል አምላክ ለልዑል እግዚአብሔር ፍቅርና በእሱም ላይ ፍጹም የሆነ እምነትና ተስፋ ሊኖረን የሚገባ ሲሆን ወደ እሱም አብዝተን ቅንነትንና እውነትን በመያዝ ትጋትን ገንዘብ በማድረግ ስለ ራሳችን ፣ ሕዝባችን ፣ ስለ ሀገራችንና ስለ ዓለማችን መጸለይን እናብዛ።

፪/ እኛ እና ህዝባችን ምን እንደምንፈልግ በመፈለግና በማወቅ ለመነሻና ለመድረሻችን ፣ ለእቅዳችንና ለግባችን ቢያንስ አብዛኛው ሕዝባችን የሚስማማበትንና ለማሳካትም በጋራ የሚሠራለትን ለሀገራችን ሕልውና እና አንድነት ወሳኝ የሆነ ግልጽና የማያሻማ ራዕይ ሊኖረን ይገባል።

፫/ ራዕያችንና ተስፋችንን ከሚያጨልሙ አያስኬድም ፣ አልተለመደም፣ አይሆንም ፣ አይሳካም የሚሉና መሠል ነቀፋዎችንና አሉታዊ የሆኑ ንግግሮችን በመስማትና ፣ ድርጊቶቻቸውንም በመመልከት ተስፋ ከመቁረጥና ከመሸበር ይልቅ በእግዚአብሔር በመመካት ይገባናል።

E.O.T.C
Far East, United Kingdom and Ireland Bishopric Office

Tel: +251 913 560713 +27 72 837 3699 +27 62 366 0579 +251 111 263527
E-mail: abbahyacob@gmail.com eotcafrica@gmail.com

አባ ያዕቆብ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሩቅ ምስራቅ ፣ ዩናይትድ ኪንግደም ፣
አየርላንድና አካባቢው ሀገራት ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እና የዓለም የሰላም አምባሳደር
Abba Yacob
Archbishop of Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Diocese of Far East, United Kingdom, Ireland and World Ambassador for Peace

ቁጥር
Ref. No. ______

ቀን
Date ጳጉሜ ፫ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም
Sep 8, 2022

፱/ሁላችንም ከአንድ ምንጭ የተገኘን የአንድ አምላክ ድንቅ የሆንን የእጁ ሥራዎች መሆናችንን በመገንዘብ ለሌሎች መልካም ማድረግን በመለማመድ፣ አእምሯችንንና ልባችንን ከቂም ፣ ከበቀል ፣ ከትዕቢትና ከእኩል ሐሳብ መቆጣጠር አለብን። ይኸውም ለሌሎች ሕዝብና አህዛብ ለራሳችንም ጭምር ሁሉ አዛኞች ፣ ደጎች፣ ሩህሩሆችና ትሁታን መሆን እንድንችል ይረዳናል።

፲/ ክፋትን ለሕዝብና ለወገን መልካም ያልሆናውን ነገር በመጸየፍ ፣ ከሌሎች ጋር እውነተኛ በሆነ ሰላም አብሮ በመኖር በጎና መልካም በሆኑ ነገሮች ላይ ሁሉ ተባብሮ መሥራትና መረዳዳት ይገባናል።

፲፩/ ምንጊዜም ቢሆን በየትኛውም ስፍራ ላይ ለሚገኝ የሰው ልጅ ሁሉ እኩል የሆነ ዋጋና ክብርን በሰውነቱ ብቻ እየሰጠን ጎሳዊ ማንነቱን ፣ ባህሉን ፣ ቋንቋውንና እምነቱን እንደራሳችን አድርገን በተግቢው መንገድ በመመልከት ማክበርና ተግባራዊ ማድረግ፣ የዳበሩ መልካምና ጠቃሚ ሀገራዊ ዕውቀቶቻችንንና ጥበቦቻችንን ካለማወቅ ከሚደረግ ማናቸውም ነገር ተቆጥበን ለጋራ እድገታችን መጠቀም ይገባናል።

፲፪/ ለተፈጥሮ በማሰብ ፣ በአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ላይ የጋራ ሃሳብን በመያዝ የሕይወታችን ሚዛን የሆኑ ዛፎችን ፣ ዕፅዋትንና ሳሮችን፣ በባህርና በየብስ የሚኖሩ አራዊትንና እንሳሳትን፣ በአጠቃላይ ፍጥረታትን ሁሉ በመንከባከብ ለፈጣሪያችን ያለንን የመጠበቅ ኃላፊነት መወጣት ይገባናል።

ሁሉን የሚችል ቅዱስ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርከን ፣ ፊቱን ያብራልን ፣ ይራራልንም !

ከአባ ያዕቆብ ሊቀ ጳጳስ ዘሩቅ ምሥራቅ፣እንግሊዝ ወአየርላንድ

E.O.T.C Far East, United Kingdom and Ireland Bishopric Office

Tel: +251 913 560713 +27 62 366 0579
+27 72 837 3699 +251 111 263527
E-mail: abbahyacob@gmail.com
eotcafrica@gmail.com